**ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት**

**1103 Amherst Avenue, Suite 2**

**Silver Spring, MD 20902**

**ታህሳስ 12 ቀን 2013 ዓ.ም.**

ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር
ዶክተር ዓብይ አህመድ
አዲስ አበባ

**የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ ከዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት (Global Amhara Coalition) የተሰጠ መግለጫ።**

በኦሮሚያ ወለጋና በቤንሻንጉል ጉሙዝ መተከል ዞን ኦነግ ሸኔና የጉሙዝ ታጣቂዎች በአካባቢው የመንግሥት መዋቅር በመደገፍ በአማራዎችና አገዎች ላይ እየደረሱት ያለዉን የማያባራ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ (Genocide) ዓለም አቀፉ የአማራ ህብረት (Global Amhara Coalition) አጥብቆ ያወግዛል::

ሽብርተኛዋ ትህነግ በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመችው ጥቃት፥በአማራው ህዝብ ላይ ያካሄደችው ወረራና በማይካድራ ያደረሰችውን የዘር ጭፍጨፋ (Genocide) እንዲሁ እጅግ አሳስቦን ቆይቷል ፥ድርጊቱ የሀገር ወንጀል ክህደት ነውም ብለን እናምናለን።

ለመሆኑ መቼ ነው የአማራው ደም እንደ ጅረት መፍሰስ የሚያቆመው?

የፌደራል መንግስት በትግራይ ያሳየውን ህግ የማስከበር ቁርጠኝነትስ ለምንድን ነው በኦሮሚያስ የማያደርገው? ለምንድን ነው በመተከል የማይደግመው?

ራሱ ማድረግ ካልቻለስ ለምን የአማራ ልዩ ኃይል መተከል በመግባት ዜጎችን ከዕልቂት እንዲታደግና ህግ እንዲያስከብር ለምንድን ነው የሚከለከለው?

ይህ ችግር ሁሉንም የመንግስት አካላት ተጠያቂ የሚያደርግ ስለሆነ በአስቸኳይ ሁኔታ ተጨባጭ ርምጃ ተወስዶ የንፁሀን አማሮችና አገዎች ደም መፍሰስ መቆም አለበት ብለን እናምናለን::

ይህ ካልሆነ ግን ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ አገርን ወደ ትርምስ ሊወስድ እንደሚችል ከወዲሁ እናሳስባለን::

በትግራይ ክልል የተካሄደው ጦርነት ሕግን የማስከበር ዘመቻ ብቻ ሳይሆን የሀገርን ሕልውና ያስጠበቀ ትልቅ ድል ነው ብለን እናምናለን።

ጦርነቱ በሰራዊቱ አኩሪ ተጋድሎና በአማራው ሚሊሺያ፣ፍኖና ልዩ ሃይል መስዋትነት በአጭር ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም ከሁኔታው ማግስት ጀምሮ ሊደረጉ የሚግባቸው ነገሮች እንዳሉ ለማመልከት አለም ዓቀፍ የአማራ ህብረት የሚከተሉትን ቁልፍ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ጥያቄወች እነደሚከተለው እናቀርባለን።

1. በኦሮሚያ ክልል በወለጋና በቤንሻንጉል ጉምዝ መተከል በመንግስት መዋቅር እየተጋዘ በማያባራ መልኩ እየተካሄደ ያለውን በአማራወችና አገወች ላይ ያነጣጠረ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(Genocide) የፌዴራል መንግስት በአስቸኳይ እንዲያስቆም እንጠይቃለን:: የዜጎችን በህይወት የመኖር መብት ማረጋገጥ የአንድ መንግስት ዋነኛና ተቀዳሚ ተግባሩ በመሁኑ ይህንኑ ግዴታወን እንዲወጣ ጥሪ እናቀርባለን።ያለበለዚያ መንግስት አለ ለማለት የምንቸገር መሆኑን አበክረን እንገልጻለን።

የኦሮሚያና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች አመራር አባላት ከዋነኞቹ እስከ ቀበሌ አስተዳደር ድረስ ያሉት ይህንን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ማስቆም አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ተባባሪዎችም ስለሆኑ በህግ እንዲጠየቁም አጥብቀን እንጠይቃለን::

2.የትህነግን ከፍተኛ አመራሮች ጁንታ ብሎ በመሰየም እነርሱን ብቻ ወደ ህግ በማቅረብ ትህነግ እንደ ፓርቲ ከነርዕዮተ አለሟ እንድትቀጥል ከተደረገ የተከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ ከንቱ የሚያስቀርና የኢትዮጵያን

ሰላምና አንድነትም የሚያናጋ ሁኔታ ስለሚፈጥር ፓርላማው በአስቸኳይ ተሰብስቦ ህወሓትንና ኦነግ ሸኔን በአሸባሪነትእንዲፈርጅም በአፅንዖት እንጠይቃለን::

3. ይህንን የሽብር ጦርነት ያስጀመሩ ፣ የመሩ ያስተባበሩ ፣የተባበሩ፣ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋና የጦር ወንጀል የፈፀሙ በጥቅሉ በዚህ የአገር ክህደትና አገር የማፍረስ ወንጀል የተሳተፉ በሙሉ በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ አጥብቀን እንጠይቃለን ::

4. ትህነግ ህገ መንግስቱ ከመውጣቱ ሀያ አመት በፊት ያለ አንዳች ህጋዊና ታሪካዊ መሰረት በጉልበት ይዟቸው የነበሩት የአማራ ርስቶች ወልቃይት፣ ጠለምት፣ ጠገዴ፣ ሁመራና እና ራያ አማራው በልጆቹ መስዋዕትነት ወደ ራሱ ይዞታነት መልሷቸዋል። በዚሁም መሰረት በእራሱ ስር የሚተዳደሩ የአካባቢ የአስተዳደር መዋቅሮችን እየዘረጋ ይገኛል:: ይህንን ሂደት በጣም የምንደግፈው ብቻ ሳይሆን አጋርነታችንም ለመግለጽ እንወዳለን:: ፌደራል መንግስት ህጋዊ እውቅና በአስቸኳይ እንዲሰጠው አጥብቀን እንጠይቃለን::

ከዚህ በተቃረነ መልኩ አዲስ በተቋቋመው የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ስር በጊዚያዊነት ይተዳደሩ ፣ ወይም በህገመንግስቱ መሰረት በወሰንና ማንነት ኮሚሽን ታይቶ ይወሰናል የሚሉት አስተያየቶች ፈፅሞ ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን እናሳውቃለን:: ህወሓት እነዚህን የአማራ ርስቶች በጉልበት ይዛ ቆይታ ወደ ትግራይ ያካለለቻቸው ህገመንግስቱ ከመውጣቱ ከአራት አመት በፊት ነው:: በህግ ሳይሆን በጉልበትና በፖለቲካ ውሳኔ የተወሰዱት ርስቶች በደም መስዋዕትነት ተመልሰዋል:፡ በመሆኑም በፖለቲካ ውሳኔ በአስቸኳይ እውቅና መሰጠት አለበት::

5. ህወሃት ከወልቃይትና ራያ አፈናቅላ ወደ ሱዳንና ሌሎች አገሮች አስደድዳቸው የነበሩትን ዜጎች ሁሉ የኢትዮጵያ መንግስት በአስቸኳይ ወደ ቀያቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች እንዲሁም ለደረሰባቸው ግፍ ተገቢ ካሳና ማቋቋሚያ መርሀ ግብር እንዲቀየስላቸውም አጥብቀን እንጠይቃለን::

6. የኦሮሚያ ብልፅግና አንዳንድ አመራሮች የአማራውን የአገር አድን ውለታ ለማኮሰስና ብሎም ራያም ሆነ ወሎ የኦሮሞ ነው የሚለው አባባላቸው አማራው 500 አመት ወደኋላ ሄዶ ጥንተ ርስቱን እንዲጠይቅ የሚጋብዝና ይህ ከሆነ ደግሞ ኢትዮጵያን ትርምስ ውስጥ የሚያስገባ ለማንም የማይበጅ በመሆኑ ከዚህና መሰል ፀረ አማራ ትንኮሳቸው እንዲታቀቡም እናስጠነቅቃለን::

7. የአማራ ብልፅግና ፖርቲ አማራውን እወክላለሁ ብሎ ነገር ግን ከጠላቶቹ ያልተናነሰ ግፍና በደል ሲያደርስበት የቆየ መሆኑ ሁላችንም የምንረሳው ጉዳይ አይደለም:: ነገር ግን ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ በተለይም ህወሓት በዕብሪት መከላከያውንና አማራውን ከወረረችበት ጊዜ ጀምሮ የአማራ ብልፅግና ፖርቲ የያዘው ጠንካራ አቋም የሚደገፍ ነው። በደሙ የተመለሱ ርስቶች በአማራ ክልል ስር ሆነው በአካባቢው ህዝብ እንዲተዳደር መደረጉ ሁሉም የአማራ ኃይሎች ተናበው እንዲሰሩ መቻሉ እንዲሁም በመተከል የሚካሄደውን ስልታዊ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ለማስቆም ልዩ ኃይሉን ለማስገባት የአማራ ብልፅግና ፖርቲ መጠየቁ በእኛ በኩል የምንደግፈውና የሚበረታታ ጉዳይ ነው:: የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ(አብን) አቋምም አማራው በደሙ የመለሳቸው ርስቶቹ እንዲከበሩለት በወለጋና በመተከል የሚካሄደው የተቀነባበረ አማራውን የማፅዳት ዘመቻ በአስቸኳይ የሚቆምበትን ሁኔታ የሚጠይቅ ስለሆነ የአማራ ብልፅግናና አብን እንዲሁም ሌሎች የአማራ አደረጃጀቶች ተባብረው እንዲሰሩ እናበረታታለን ::

8. በሸዋ የደራ አማራ ማንነቱ እንዲከበር በተወካዮቹ በኩል ጥያቄ በማቅረቡ እየተሰደደ ይገኛል:: የአማራ ብልፅግናና አብን ይህንንም የአማራውን የማንነት ጥያቄ መልስ እንዲያግኝ ተባብረው እንዲሰሩ እንጠይቃለን::

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለኦሮሚያ ብልፅግና ጥያቄ አለን?

ምነው ወሎ ድረስ ሄዶ የራሱ የዞን አስተዳደር ያለውን የከሚሴን ኦሮሞ ጉዳይ ለማንሳት ሲከጅል በራሱ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የደራን ፍትሀዊ የሆነ የማንንት ጥያቄ ማየት አልቻለም?

እንዲሁም ለምንድን ነው እንደ አማራው ክልል ሁሉ በኦሮሚያ የሚኖሩ ከ15-20 ሚሊዮን የሚሆኑ አማሮችና ሌሎች ኢትዮጵያውያን የራሳቸው መስተዳደር እንዲኖራቸው የማያደርገው? ይህ በአስቸኳይ መልስ እንዲያግኝ እንጠይቃለን። በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለዉ ግልፅ የሆነ የተረኝነት አካሄድ በጣም አሳስቦናል:: አስቸኳይ መልስም የሚሻ ጉዳይ ነዉ::

9. በወለጋና በመተከል የሚኖሩ አማሮችና አገወች በየጊዜው ከሚደርስባቸው ጭፍጨፋ ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና አካባቢያቸውን መጠበቅ እንዲችሉ መንግስት የማስታጠቅ ግዴታ አለበት:: መፍትሄ የሚያመጣ ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲያስታጥቃቸውም እንጠይቃለን::

10. ኢትዮጵያን ለዚህ ሁሉ የፖለቲካ ምስቅልቅል የዳረጋት ህወሓት ህዝብን ከፋፍላ ለመግዛት በተንኮል የቀረፀችው ህገ መንግስት ዘርን መሰረት አድርጎ የተዋቀረው የጎሳ ፌደራሊዝምና ክልል መሆናቸውን ህዝብ ሁሉ የተረዳው እውነታ ነው።ስለዚህ ህወሓትን አስወግዶ ራሷ ለተንኮሏ የፈጠረቻቸውን ግሳንግስ ተሸክሞ መዝለቅ በተጠመደ ፈንጅ ላይ እንደመረማመድ ስለሚቆጠር በአሁኑ ጊዜ ምርጫ ለማካሄድ ከመሯሯጥ ይልቅ እጅግ አሳሳቢው ጉዳይ አዲስ ህገ መንግስት የመቅረፁ ሂደት በአስቸኳይ እንዲጀመር እንጠይቃለን፡:

በአዲሱ ህገ መንግስት ለህዝብ መተላለቂያ እንዲሆን የተሰራው ክልል ፈርሶ በሌላ ተቀባይነት ባለው የፌደራል አወቃቀር መተካት አለበት። ዘርንና ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋምም በህግ የታገደ ሊሆን ይገባል።

እንዚህንና መሰል ድርጊቶች ከተከናወኑ በኋላ ለምርጫ መዘጋጀት ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ በር ይከፍታል ብለን እናምናለን: ይህም ለኢትዮጵያ ህዝብ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ፅኑ መሰረት ስለሚጥል ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል።

ዓለምአቀፍ የአማራ ህብረት (Global Amhara Coalition) የኢትዮጵያ መንግስት ከላይ ላቀረብናቸዉ አገራዊና ሰብዓዊ ፋይዳ ላላቸዉ ጥያቄወች አስቸኳይ አወንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ አጥብቆ ይጠይቃል።

ኢትዮጵያንና ህዝቧን እግዚአብሄር ይባርክ፣ ይጠብቅ!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጀግንነትና መስዋዕትነት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት (Global Amhara Coalition)

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር
አምባቸው ወሮታ (ዶ/ር)
የአለም ዓቀፍ አማራ ህብረት ሊቀ መንበር

rግልባጭ
ለክብርት የኢፌዴሪ ፕሬዜዳንት ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘዉዴ
ለተከበሩ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን

ለተከበሩ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ
ለክብርት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ
ለተከበሩ የአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር አቶ አገኘሁ ተሻገር
ባሕርዳር
ለተከበሩ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባስደር አቶ ፍጹም አረጋ
ዋሽንግተን ዲሲ
ለተከበሩ ለሰብአዊ መብት ጉባኤ አቶ ቢኒያም አባተ አዲስ አበባ
ለተከበሩ ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለማርያም
ብረሰልስና ጄኔቫ